# ዓለም፣ ዓለሚቱ…



ጭንቄ እጅግ ቀልሎኝ፣ ፍርሓቴም ተሽሎኝ፣
ልጅነት፣ ሞኝነት፣ በጣሙን ደስ ብሎኝ፣
ገባሁ፣ ተታልዬ…
ዓለም ሰላም መስሎኝ!

ዓለም በዕልልታ፣ ፊቷንም አብርታ፣
በእምብልታ፣ መለከት፣ ሰግዳ፣ ተርበትብታ፣
እያለች፤ "ውድዬ!"…
በብዙ ውካታ!



ኣንቃ እየሳመች፣ በዓይኗ እያባበለች
ሞሰቡን ዘርግታ፣ በፍቅር ዓይን እያየች
አጉርሳ፣ አስተናግዳኝ…
ጠጁን አጠጣችኝ!



በመርዟ፣ ሰክሬ፣ ጭንቅላቴ ዞሬ፣
ኪሴ ባዶ ሲቀር ፍጥጥ አልኩ አፍሬ፣
ይዛ፣ አዋርዳኝ…
ወጣሁ ተሽቀንጥሬ!

ራሴን እያዞረኝ፣ ያን ሁሉ ጠጥቼ፣
ልራመድህ ብለው ከደጅ ወጥቼ፣
መሬት ራሱ ከዳኝ!
ጕዳናውን ስቼ…

አለሁኝ፣ ደህና ነኝ፣ ቆሜያለሁኝ ስል
ተንሸራተትኩና፣ ገባሁኝ ገደል
ዲንጋዩ ባሰብኝ…
ምን ዓይነት ዕድል!



አየ ሕይወት መጥፎ፣ ልክ አለማወቅ
ድንገት ተንከባልሎ ከጭቃ መውደቅ
ምነው በቀረብኝ…
ወይ መጨማለቅ!

ገ/ኢ. ጕርፉ።